## ፲፫

# ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችን ስለ ማስተማር

### ዕውቀትን ማጣት

እስከዚህ ደረስ መጽሐፍ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት አድርገን ማስተማር እንዳለብን ማጥናት ችለናል:: ቀጥለን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማይመጡ ሰዎች እንዴት ልናስተምራቸው እንደምንችል እንመለከታለን:: ዓላማችን በሳምንት አንድ ቀን የጥናት ክፍለ ጊዜ ማዘጋጀት ነው፤ ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወንጌልን አብራርተን እንድናስተምር ያስችለናል:: ታዲያ ይህን የመሰለውን የጥናት ክፍለ ጊዜ ከመጀመራችን በፊት በጥናቱ ላይ የሚሳተፉ ሰዎችን ማግኘት ይኖርብናል:: ይህ ምናልባት ቀላል አይሆንም ይሆናል::

ብዙ ሰዎች ሃይማኖት እንደሌላቸው ቢናገሩም እንኳ አንድ ዐይነት እምነት በውስጣቸው ሊኖር ይችላል:: ይህም የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕርዩ እንደ ሆነ ያመለክታል:: በመሠረቱ ሰዎች በእግዚአብሔር ቢያምኑም ባያምኑም ስለ ሃይማኖት አጥርተው መናገራቸውን ይጠራጠራሉ::

ይህም የሚታየው በስም ክርስቲያን በሆኑ አገሮች ውስጥ ጭምር ነው:: ብዙ ሰዎች ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ማወቅ እንዳለባቸው ይሰማቸዋል፤ ችግሩ ግን ሊረዷቸው የሚችሉትን ሰዎች ለመጠየቅ አይደፍሩም፣ ቢጠይቋቸውም አልፎ አልፎ ነው:: ስለ ክርስትና አጥጋቢና ጠቃሚ የሆነ መረጃ የሚገኘው ከቤተ ክርስቲያንና ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ቢሆንም ብዙ ሰዎች ይህን ማድረግ አይፈልጉም:: እነዚህ ሰዎች ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው አስተሳሰብ በጣም አናሳ ስለ ሆነ የፈለጉትን ጠይቀው መማር አይችሉም:: ሆኖም እንዲህ ካሉ ሰዎች ጋር ጓደኝነትን ብንመሠርትና ስለ ክርስትና ብንገልጽላቸው ፈቃደኞች ሊሆኑ ይችላሉ::

### ወዳጅነትን መመሥረት

ችግሩ ብዙ ክርስቲያኖች ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር መወዳጀትን ይፈሩታል:: የኢየሱስን ሕይወት ስናጠና ግን ምን ማድረግ እንዳለብን ማለፊያ መመሪያ ሊሰጠን ይችላል:: ስለሆነም የክርስትና ሕይወታችንን ሳናዋርድ፥ የሕይወት መመሪያዎቻችንን አሳልፈን ሳንሰጥ፥ የወንጌልን ክብር ዝቅ ሳናደርግ ልናገለግል እንችላለን:: ከሰዎች ጋር እንዴት አድርገን መወዳጀት እንደምንችል ለማስተማር ይህ መጽሐፍ ስፍራው አይደለም፤ ሆኖም ሰዎችን ወዳጆች ለማድረግ የሚፈለገውን መሥዋዕትነትን መክፈል አለብን:: እንዲህ ማለትም ከልባችን

አስበንበት ሰዎች ወደ ጌታ እንዲመጡ ለመርዳት እንጂ የመስበክ ዕድል ለማግኘት ኅብረት እንፍጠር ማለት አይደለም። ራሳችንን ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች በመለየት ፈንታ ወዳጆቻቸው እንሁን። ጌታ ኢየሱስ «የኀጢአተኞች ወዳጅ» እንደ ሆነ ይታወቅ ነበር፤ ይህ ድርጊት በሃይማኖት አክራሪዎች ዘንድ የተነቀፈ ነበር፤ በአንጻሩ ግን ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ያመጣ ኢየሱስ እንጂ ከሳሾቹ አልነበሩም፤ (ማቴ 11፥19 ፤ 21፥31)።

ሰዎችን ወዳጆቻችን ለማድረግ በምንነሣበት ጊዜ የሕይወታችንን ሁኔታና አካሄዳችንን ማስተካከል ይኖርብናል። ለማድረግ በምንፈልጋቸው ነገሮች ዙሪያ ሕየወታችንን ከማደላደል ይልቅ ከሌሎች ጋር ለመስማማት መሥዋዕትንትን መክፈልና መለወጥ ይኖርብናል። ሰዎችን ለመርዳት ከምናደርገው ጥረት ሌላ እነርሱም እንዲረዱን ልንጠይቃቸው እንችላለን። ሰዎች እኛ ብቻ በተከታታይ መልካም ነገር ብናደርግላቸው፥ እነርሱ ግን እንዲያደርጉልን ዕድል ባንሰጣቸው ይጠራጠሩናል። ስለዚህ እነርሱን ወዳጆቻችን ለማድረግ መጣር ያለብን እኛ ብቻ ሳንሆን እነርሱም ለእኛ የሚቻላቸውን እንዲያደርጉ መስማማት ያሻናል።

አንዳንድ ጊዜ እነዚህን የወዳጅነት ሁኔታዎች እንዴት አድርገን እንደምንጀምር አናውቅም። አንዱ መንገድ በኅብረተሰቡ ቡድኖች ውስጥ መግባትና በተግባር እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ ነው፤ በትምህርት ቤቶች፥ በጤና ጉዳዮች፥ በስፖርት፥ በባህላዊ እንቅስቃሴዎችና በማኅበራዊ ተግባራት ሁሉ መሳተፍ ይቻላል። ደግሞም ከጎረቤቶቻችን፣ ከዘመዶቻችንና ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር ወዳጅነትን መመሥረት እንችላለን።

ሁላችንም ራሳቸውን ያልሰጡ፥ እንዲያውም ወንጌልን የማያውቁ ክርስቲያያኖች የሚገኙባት ቤተ ክርስቲያን አባላት ነን። አብያተ ክርስቲያን ቤተ ክረስቲያን አልባ ከሆኑ ቤተ ሰቦች የመጡ ወጣቶችና ልጆች የሚሳተፉባቸው ሳምንታዊ ፕሮግራሞች አሏቸው፤ እኛም ከወላጆቻቸው ጋር ትውውቅ መጀመርና ጓደኝነትን መመሥረት እንችላለን። እነዚህ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ለልጆቻው በምታደረገው አገልግሎት ደስተኞች ናቸው፤ ንቃቱ ካለን በቤታቸው ማነጋገር የምንችልባቸው ዕድሎች አሉን። በበኩላችን በምናደርገው ጸሎትና ትጋት ጭምር ባጭር ጊዜ ውስጥ ኅብረታችን ይመሠረታል። በምናዳብረው ወዳጅነትና መግባባት አማካይነት ቀስ በቀስ በቤታቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጀመር እንችላለን።

በመነጋገር ላይ ያለነው ወንጌልን በመካፈል ፅንሰ ሐሳብ ለአንድ ጊዜ በተገኘ ዕድል እዚህና እዚያ መመስከር አለብን አይደለም። ስለእምነታችን መናገር መወላወል አለብን ማለትም አይደለም። እንዲያውም ስለ እምነታችን በቀጥታ መግለጽና ከተቻለም ለወዳጆቻችን ስለ ድነት በቀላሉና በግልጽ የሚያስተምር መጽሐፍ መስጠት አለብን። (እንዲህ ካሉት መጻሕፍት አንዱ «የክርስቲያን እምነት» ከገጽ118-119 ይመ)። ይህም የረጅም ጊዜ ዓላማችን ሲሆን፥

በሚመደቡት ሳምንታት ስለ ክርስትና መሠረታዊ ዕውቀት በመናገር በትዕግሥትና በጥንቃቄ የምንጓዝበት ጊዜ ነው። ትምህርቱን የምንሰጥበት መሳሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች ቤት

ወንጌልን ለማሰራጨት ስለሚያስችሉን መመሪያዎችና ዘዴዎች፥ እኛም ለሥራው ራሳችንን በመንፈስና በተግባር እንዴት እንደምናዘጋጅ ብዙ ተጽፏል። ስለ ሆነም አንባቢዎች ወንጌልን በግል ስለ ማሠራጨትም ይሁን ስለ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ እነዚህን የመሰሉ ጽሑፎች ቢመለከቱ ይጠቅማቸዋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በነዚህ ጉዳዮች ላይ በዝርዝር ለመነጋገር ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ላላመኑ ሰዎች ስለምናስተምርበት መንገድ ትኩረት ለመስጠት ነው።

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በምናስብበት ጊዜ «የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት» ብለን በዚህ ርእስ ለወዳጆቻችን ልንነግራቸው አያስፈልግም፤ አንድ ለየት ያለ ስም ልናወጣለትም አይገባም፤ ምክንያቱም ሰዎች ወደ አንድ ዐይነት ሃይማኖት ሊያስገቡን ነው ብለው እንዲጠረጥሩን አንፈልግም። ብዙ ሰዎችም ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት ክርስቲያን ያልሆኑበት ምክንያት ስለ ክርስትና እምነት የሚያውቁት ትንሽ ከመሆኑ የተነሣ መሆኑን ስለሚገነዘቡ ልናካሄደው ስላሰብነው ጥናት ብንገልጽላቸው ደስተኞች ናቸው። አንድ መጽሐፍ አብረውን ካጠኑ በኋላ ክርስትና ምን ማለት እንደሆነ ራሳቸው እንዲደርሱበት እንሻለን።

ጥናቱ በሳምንት አንድ ጊዜ፥ ለስድስት ሳምንታት የሚቀጥል መሆኑን ለሰዎች ልናሳውቃቸው ይገባል፤ ይህን ሲገነዘቡ በጊዜ ባልተወሰነ ጥናት ውስጥ ታስረው የሚቆዩ አለመሆናቸውን ያረጋግጣሉ። እያንዳንዱ ጥናት ለአንድ ሰዓት ብቻ ይሰጣል። የሰዎቹ ፍላጎት እያደገ ሲሄድና በጥናቱ ወቅት የሻይ ግብዣ ካለ ከአንድ ሰዓት በላይ ሊራዘም ይችላል።

የሚቻል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ገና ክርስትናን ያልተቀበሉ ሰዎች ቤት ውስጥ መምራት ይቻላል። እንዲያውም ጥናቱ በቤታቸው ውስጥ ቢካሄድ ያለሥጋት ሊያጠኑ ከመቻላቸውም በላይ ጊዜ ሳያባክኑ መገኘት ይችላሉ። የጥናት ቡድኑ አባላት ጥቂት መሆን አለባቸው፤ የተጋቡ ሰዎች የሚገኙበት ከሆነ ጥናቱን መጀመር የሚቻለው ባሎች በጥናቱ ላይ ሊገኙ ከቻሉ ነው። ይህን ስናደርግ ወንዶቹ ከጥናቱ እንዳይቀሩ፤ በባልና በሚስት መካከል ችግር እንዳይፈጠር እንጠብቃለን።

ሌላው ማረጋገጥ ያለብን የጥናት አባሎቻችን ቤታቸውን ትንሽ ቤተ ክርስቲያን አድርገን እንዳንጠቀምባቸው ነው፤ ስለሆነም በቤቱ ውስጥ ጸሎት፥ መዝሙር፥ የሃይማኖት መግለጫ፥ ስርዐተ ኑዛዜ አይደረግም፤ ጥያቄ አይጠየቅም፤

መልስም አይመልሱም፣ የፈተና ወረቀትም አይቀርብላቸውም:: ዐላማችን ሰዎችን ጥያቄ በመጠየቅና ዕውቀታቸውን በመፈተን መያዝ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅመን ወንጌልን ግልጽና ቀላል በሆነ መንገድ ማስተማር ነው::

## ወንጌልን የሚያብራራ መጽሐፍ

የክርስቲያንን እምነት ደረጃ በደረጃ ከሚያብራሩ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል አንዱና ልንጠቀምበት የሚገባው መጽሐፍ፥ የሮሜ መልእክት ነው:: ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችን ለማስተማር በሮሜ መልእክት ተጠቀሙ በምንልበት ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች ይደነቁ ይሆናል:: የዚህ ምክንያቱ ያመኑ ክርስቲያኖችም ቢሆኑ የሮሜ መልእክት ከባድ ሆኖ ስለሚያገኙት ነው:: አብዛኛዎቹ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች አንዱን መጽሐፍ ከሌላው አይለዩም:: በአኳያውም የሮሜ መልእክት ከባድ መጽሐፍ ነው ብሎ የነገራቸው ሰው ስለሌለም በመማር ረገድ የተሻለ ዕድል አላቸው:: ውጤት ሊገኝበት የሚችለው ሁኔታ የሚታየው መጽሐፉን ለማብራራት በምናደረገው ጥረት ነው:: የእኛ ዐላማ ቃላትን ሁሉ መተርጐምና ማብራራት ሳይሆን ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌሉ ላይ የሰጠው ማብራሪያና ትምህርት ከእኛ ጋር እንዲዋሃድ መፍቀድ ነው::

በጥናት ቡድኑ ውስጥ ያሉ አባላት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ስለ ወንጌል ጥቂት ያውቃሉ ብለን ግምት ቢኖረንም ለምን የበለጠ አላወቁም ወይም አያውቁም ብለን በንቀት ልንናገራቸው አይገባም:: በቀላልና በግልጽ ቋንቋ መናገር ማለት ግድየለሽ ወይም የጅል አነጋገር መሰንዘር ማለት አይደለም:: ከባድ ያልሆነና የተለመደ ቃል በመናገር መንፈሳዊ ትምህርት ለመቀሰም ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች እንደ በሳል፥ አዋቂና ምሁር ቈጥረን ማነጋገር አለብን:: ስለሆነም ሰዎችን በዚህ ሁኔታ ካስተናገድናቸውና ቀደም ሲል ያላወቁትን ትምህርት እያብራራን ካስተማርናቸው በደስታ ይቀበሉታል::

ለስድስት ሳምንታት በምንሰጠው ጥናት ብቻ የሮሜን መልእክት ልንፈጽመው አንችል ይሆናል:: ብዙ ጊዜ በልምምድና በተመክሮ እንዳየነው አብዛኛዎቹ ሰዎች ጥናታቸውን ከስድስት ሳምንታት በኋላ አያቆሙም:: ስለዚህ፥ ፍላጎታቸው የተነሣሣ ስለ ሆነ የጀመሩት መጽሐፍ እስኪፈጸም ድረስ መቀጠል ይሻሉ:: ሆኖም ጥናታችን እስከ ምዕራፍ 6 ከዘለቀ በዚህ ጊዜ ውስጥ ወንጌልን ለማስተማር ብዙ ዕድል አግኝተናል ማለት ይቻላል:: እስቲ ለሁሉም ቀጥለን ይህ በምን አኳኋን እንዲተገበር ባጭሩ እንከታተል::

ምዕራፍ አንድ እግዚአብሔር መኖሩን ይነግረናል:: ይህ ሆኖ ሳለ እኛ ግን በእርሱ ላይ በማመፃችን ምክንያት በኀጢአት ውስጥ ወድቀናል:: ከዚህ የተነሣ የእግዚአብሔርን ፍርድ በራሳችን ላይ አመጣን፤ ይህም ሁኔታ አረማውያን ብንሆን (ልክ በጳውሎስ ጊዜ እንደ ነበሩ አሕዛብ) ወይም እግዚአብሔርን ከሚፈራና

ከተከበረ ቤተ ሰብ የመጣን ብንሆን (ይህም በጳውሎስ ዘመን እንደ ነበሩት አይሁድ)፥ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ወድቀናል፤ ምዕራፍ 2 ይህን ሐቅ ግልጽ ያደርገዋል። ስለዚህ በራሳቸው ጽድቅ የመመካት ባሕርይ ወይም የሃይማኖታቸው ሥነ ሥርዓት አያድናቸውም ይላል። የምዕራፍ 3 የመጀመሪያ አጋማሽ ለምዕራፉ ትልቅን ትምህርት ሲሰጥ ሁላችንም በደለኞች (ኀጢአተኞች) ስለ ሆንን ራሳችንን ለማዳን የምናደርገው ነገር የለም ይላል።

እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ 3 ቍጥር 21 ላይ ሲናገር »አሁን ግን እግዚአብሔር በደለኛውን ኃጢአተኛ እንዴት አድርጎ ከራሱ ጋር እንደሚያስታርቅ አሳይቷል»፤ ይላል። ይህንንም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በጸጋ ያደርገዋል የምሕረቱንም ስጦታ በእምነት እንቀበላለን። ድነት በመልካም ሥራችን፥ የሃይማኖት ሥነ ሥርዓቶችን በመፈጸም፥ ሕግን በመጠበቅ አይደለም፤ ድነትን ማግኘት የምንችለው በእምነት በጸጋ ብቻ ነው። ጳውሎስ ይህንንም በምዕራፍ 4 ላይ በተለያዩ ስፍራዎች ገልጾ አስተምሯል። ከዚያም በመቀጠል በምዕራፍ 5 ላይ አማኞች እንዴት አድርገው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንደሚኖራቸውና እንዴት የዘላለም ሕይወት ዋስትና እንዳገኙ ይናገራል። ይህም ለአማኞች የተረጋገጠ ነው። ምክንያቱም፣ ኀጢአታቸው ምንም ያህል ትልቅ ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ኃጢአታቸውን ለመሸፈን ምን ጊዜም ብቃት አለው።

ይህ ትምህርት ተቃውሞን ያስከትላል፤ ተቃውሞውም ድነት በእምነት በጸጋ ብቻ የሚገኝ ከሆነ በጣም የቀለለ ይሆናል፤ ሰዎች እንደ ፈለጉ ኀጢአት ሠርተው እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው ይቅርታን እንዲለምኑ ያበረታታቸዋል የሚል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ 6 ላይ መልስ ይሰጥና በምዕራፍ 7 እና 8 ላይ አማኞች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያስተምራል።

ይህን መጽሐፍ የሚያስተምረው መምህር የተሰጠውን የመጽሐፉን ማብራሪያና መመሪያ ተከትሎ፥ በዚህም ክርስቲያን ያልሆኑትንና ክርስቲያን የሆኑትን አብሮ በማስተባበር፥ ተቀባይነት ያለውን ርእስ ጉዳይ ያስተምራቸዋል። ይህ ግልጽ ማጠቃለያ እንደሚያመለክተው ግን በጥናታችን የመጀመሪያዎቹን ስድስት ምዕራፎች ብቻ ብንሸፍንም፥ በጥናቱ ላይ ወንጌልን በግልጽና ኀይልን በተሞላ መንገድ እናቀርባለን። እዚህ ላይ የሚያጋጥመን ችግር እንዴት አድርገን ዝርዝር ጉዳዮችንና ሌሎች ሁኔታዎችን አስወግደን የእነዚህን ምዕራፎች ይዘት እንደምናብራራ ነው።

## ጥናትን ስለ መጀመር

ባካሄድነው የመስብክና የማስተማር ሥራ ላይ እንደተገነዘብነው ለስኬት ቍልፉ ርእስ ጉዳዮችን በሚገባ ማወቅ ነው። የሮሜን መልእክት ይዘት በሚገባ በማጥናት ያላንዳች ችግርና ሥጋት ልንወጣው እንችላለን። ይህን ጥናት

ለማካሄድ የምናደርገውን ዝግጅት ሌላ ማንም ሰው ሊሠራልን አይችልም:: የሚከተለው አስተያየት የሮሜን መልእክት ለዚህ መጽሐፍ አንባቢዎች ለማስተማር አይደለም:: ዐላማው፥ ሐሳቡ ከሰው ወደ ሰው ለምናደርገው ጥናት እንደ ዘዴ ሆኖ እንዲያግዘን ነው:: ሐሳቡ ወይም አስተያየቱ በሮሜ መልእክት አጠቃቀማችን ላይ የተመሠረተ ሲሆን የምንጠቀምበትን መርሕ ግን በሌላም በምናስተምረው መጽሐፍ ላይ ልንገለገልበት እንችላለን::

ስለዚህ በሮሜ መልእክት ላይ ጥናቶችን ከማካሄዳችን በፊት መጽሐፉን በተመለከተ ስለ አመጣጡ ታሪክ ብናብራራ ማለፊያ ነው:: የጥናት ቡድኑ አባላት ጊዜያቸውን በስድስት ሳምንታት ባይወስኑ የመጀመሪያውን ጥናት ለመላው መጽሐፍ ቅዱስ ማስተዋወቂያና መግቢያ አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ብዙ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ሁኔታ ማወቅ ይፈልጋሉ:: ስለዚህ በዚህ ዕድል በመጠቀም ኢየሱስ የዚህ ታሪክ ማዕከል መሆኑን እንዲገነዘቡ ልንረዳቸው ይገባል:: ብሉይ ኪዳን ወደ እርሱ የሚመራን ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ ከእርሱ ውስጥ ፈልቆ የሚፈስ ነው::

የመክፈቻውን ጥናት በዚህ መንገድ ልንጠቀምበት ባንችል የክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ የተባለውን ትንሽ መጽሐፍ ቅጂዎችን ልናድላቸው እንችላለን:: ይህን መጽሐፍ በቤታቸው ሊያነቡ ይችላሉ:: ይህ መጽሐፍ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ቅኝት ያደርጋል:: ከዚህም ጋር መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደ ተጻፈ ሰዎች የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ:: ለምሳሌ (ሰዎች በምን ምክንያት ሽባ ሆነው ይወለዳሉ? መሬት ለምን ይርዳል? ረሀብ ለምን ይኖራል? ወዘተ) ጥያቄዎቹ አጠቃላይ የሆነ መንፈስ ቢኖራቸውም ለመመለስ መሞከር አለብን:: መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ጥያቄ ሁሉ መልሱን ይሰጣቸዋል የማለት ግምት ስላላቸው ለአንዳንድ ጥያቄዎች ቁርጥ ያለ መልስ ያላገኘንላቸው መሆናችንን ግልጽ አድርገን ብንነግራቸው እፎይታ ያገኛሉ:: ይህን ስንነግራቸው ብድግ ብሎ ለሚጠየቅ ጥያቄ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የመልስ ምንጭ አለመሆኑንና የእግዚአብሔር ድነት መገለጥ መሆኑን ለማስገንዘብ ዕድል እናገኛለን::

ሰዎች የፈለጓቸውን ጥያቄዎች ቢያነሡም በበኩላችን የምንወያይበት በቂ ጊዜ ሊኖረን ይገባል:: እዚህ ላይ ሰዎች እኛ ለመጽሐፍ ቅዱስ ከመንሰጠው አክብሮት ያነሰ ሁኔታ ቢየሳዩን ልንደነግጥም ሆነ ልንበሳጭ አይገባም:: በዚህ ጊዜ እኛ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለንን አስተሳሰብ በእነርሱ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ ሳይሆን ሰዎቹ የሮሜን መልእክት እንዲያነቡ ማስቻል ነው:: መጽሐፉን ማንበብ ከጀመሩ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ እንዲናገር እንተውዋለን::

ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ማን እንደ ሆነ ያውቃሉ የሚል ግምት ሊኖረን አይገባም:: እርሱን ለሰዎች ስናስተዋውቅ በክርስቶስ ጊዜ አማኝ ባይሆንም ኋላ አምኖ የእንደኛው ምዕተ ዓመት መሪ፥ የወንጌል መልእክተኛ፥ አስተማሪ

ሊሆን መቻሉን ልንገልጽላቸው ይገባል፤ ከዚያም ያደረጋቸውን ጉዞዎች ለማሳየት በካርታ እንጠቀማለን:: ቀጥለንም የበፊት ታሪኩን ለመግለጽ ወደ ሐዋርያት ሥራ 19 እና 20፥ ሮሜ ምዕራፍ 1 እና 15 እናመራለን:: ስለ አስፈላጊ ቦታዎች፥ (ስለ ግሪክ ፥ ኢየሩሳሌም፥ ሮም፥ ስፓኝ)፥ የሚናገሩ ጥቅሶችን በመምረጥ ስለ ጳውሎስ አጠቃላይ የጉዞ ሁኔታ ማመልከትና መልእክቱን የጻፈበትን ምክንያት መግለጽ እንችላለን::

ሰዎች እውነተኛና ቀጥተኛ የሆኑ ዝርዝር ትምህርት በደስታ ይቀበላሉ:: በአንጻሩ ብዙ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ግንዛቤ የተምታታ ነው:: ከዚህ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስን እንደተረትና የወግ መጽሐፍ ይቈጥሩታል:: ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ከገሃዱ ዓለም ጋር የሚያስተሳሥረውን እውነታ ሊገነዘቡ ይችሉ ዘንድ ሐሳባቸውን ወደ ትምህርቱ ለመሳብ መቻል አለብን:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ጀርባ ላይ ካርታ ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን የሐዋርያው ጳውሎስን ጉዞ ለመግለጽ ከሌላ ስፍራ ፈልገን በካርታ መጠቀም አለብን:: ልጆች በትምህርት ቤት የሚጠቀሙበትን ካርታም መዋስ እንችላለን:: ይህም ባይሆን በናሽናል ጂኦግራፊ ካርታ መገልገል ይቻለናል:: ዓላማችን እነዚያ ቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበሩና በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ የተገለጹ ስፍራዎች ዛሬም ያሉ መሆናቸውንና ከዛሬው ዓለም ጋርም ለማያያዝ ነው::

አብዛኛዎቹ ሰዎች ስለ ኔሮ የሰሙ በመሆናቸው ይህ ንጉሥ በሮም በነገሠበትና ንጉሥ በነበረበት ዘመን፥ በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች የሐዋርያው ጳውሎስን መልእክት የተቀበሉ መሆናቸውን መግለጽ እንችላለን:: ይህም መግለጫ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ኔሮ የታሪክ ሰው እንደ ነበረ እንዲያስቡ ያግዛቸዋል::

**በትክክኛው አቅጣጫ መጓዝ**

በዚህ በመክፈቻ ጥናታችን፥ የቻልነውን ያህል ተጉዘን መጽሐፉን ማጥናት አለብን:: በዚህ አጋጣሚም ሰዎች የሚያነቡትን እንዲገነዘቡና ጥናታችንም ትምህርት ሰጪ መሆኑን እንዲያስተውሉ እንፈልጋለን:: አብዛኛውን ጊዜ ለአንባቢዎቻችን ዕይታ ቦግ ብለው የሚታዩ ፊደላት ያሉት መጽሐፍ ቅዱስ ያሻናል:: የሚቻል ከሆነ አንድ አንባቢ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ቢኖረው የተሻለ ነው:: በአኳያውም መደበኛ ትርጉም ቢኖራቸው ማለፊያ ነው:: እንዲህ ያለ አሠራር በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላለው ጥቅስ እያይዘን መወያየት እንችላለን::

አብዛኛው ጥናታችን የሚያተኩረው የምንባብ ክፍልን ማብራራት ስለ ሆነ የሚበልጠውን ማብራሪያ የምንሰጠው እኛ ብንሆንም ጥቂት ቃላትን እንዲያነቡ ዕድል ብንሰጣቸው ራሳቸውን የጥናቱ ተካፋይ አድርገው ይቈጥራሉ:: ይህ አካሄድም የሰዎችን የማንበብ ችሎታ ለመገንዘብ ያስችለናል:: ማንበብ

የማይችሉትን ሰዎች ማንበብ ባለመቻላቸው ቅር እንዳይሰኙ ብዙ እንዲያነቡ አንጠይቀቸውም፣ በአንጻሩ ችሎታ ካላቸው የበለጠ እንዲያነቡ እናበረታታቸዋለን።

በምዕራፍ አንድ በመጀመሪያዎቹ ዐሥራ አምስት ጥቅሶች ላይ ጊዜያችንን መፍጀት የለብንም። እነዚህን ጥቅሶች አብዛኛዎቹን በመልእክቱ መግቢያ ታሪክ ላይ አንብበናቸዋል። ስለዚህ ወደ ቊጥር 16 እና 17 ልንገዝ እንችላለን። እነዚህ መላውን መልእክት ለመገንዘብ ቊልፍ ሚና አላቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ውስጥ ምን እንደሚሠራ ነቅሰን ማየት አለብን። እርሱም እግዚአብሔር ሰውን ከራሱ ጋር እንዴት እንደሚያስታርቅ ይገልጻል። በማንኛውም ዘመን፥ በማንኛውም አገር እግዚአብሔር የሚያድናቸው እርሱ በንስሐና በእምነት ወደ የሚመጡትን ነው፤ (ሮሜ 10፥13)። ወንጌልም እግዚአብሔር ይህን በምን አኳኋን እንደሚፈጽም፥ ከተግባር በስተጀርባ ምን እንዳለ ይገልጻል። በአጽንዖት ብንናገር፥ የሮሜ መልእክት የሚያስተምረው የክርስቲያንን የአኗኗር ሁኔታ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ወይም መልእክት ውስጥ ደጋግመን የምናገኛቸውን ጠቃሚ ቃላት፦ «ወንጌል»፥ «ድነት»፥ «እምነት» ፥ «ቅድስና»፥ «ጽድቅ»፥ «ጸጋ» እና በተለያዩ ትርጒሞች ውስጥ ያሉ አቻ ቃላትን ለጥናት ቡድኑ አብራርተን ማስረዳት አለብን። ሰዎችን ግራ ሳናጋባ ቃላቱን ቢያንስ በትክክል ማስተዋወቅና በሚቀጥሉት ምዕራፎች ላይ በዝርዝር የሚያብራራልንን የድነት ዕቅድ አጭር መግለጫ መስጠት ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦችን ሰፋ አድርጎ ማቅረብ አያሻም፣ ግን መጽሐፉ ወደየት እንደሚያመራ ሰዎች ማወቅ ይፈልጋሉ። እኛም የምናደርገው ጥናታችን ወደየት አቅጣጫ እንደሚያመራ አቅጣጫውን በማሳየት መርዳት ሲሆን በአቅጣጫው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ መልእክቱን ሊያስተላልፍ የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸት ነው።

ስናስተምር የማስታወሻ ደብተር ሊኖረን ይገባል። በማስታወሻችንም በጥናታችን ውስጥ የሚገጥሙንን ቃላት ወይም የሚሰማን አስተያየት (ለምሳሌ፦ እምነት= መመኪያ፥ መታመን፥ ሃይማኖት) በተሰኙት ቃላት ላይ መስመር፥ ቀስት ቊጥር ልንጽፍ እንችላለን። ጥናቱን በምናጠናቅቅበት ጊዜ ማስታወሻችን ብዙ ቁምነገሮችንና ነጥቦችን ይዞ እናገኘዋለን። የቡድኑ አባላት ማስታወሻውን ወስደው ኮፒ ማድረግ ወይም ማስቀመጥ ይፈልጋሉ። ሳምንታት እያለፉ ሲሄዱ የሰበሰቧቸው ማስታወሻዎች ጠቃሚ መሣሪያዎች ሆነው ያገኟቸዋል።

**ከግንዛቤ በላይ**

ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር የሮሜን መልእክት ስናጠና የምናገኘው አንድ ጒድለት፥ እኛ ኢየሱስን በወንጌሉች እንዳቀረብነው አያገኙትም። የሮሜ መልእክት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር እንዴት እንዳያስታረቀን ይነግረናል፤ (ይህን ያደረገው በኢየሱስ በኩል ነው)፤ ኢየሱስ በዓለም ውስጥ በመኖር ለኀጢአት

በመሞት፥ ከሙታን በድል በመነሣት ተልእኮውን እንደ ፈጸመ ለማየት ግን ወደ ወንጌሎች መሄድ አለብን። የወንጌሎች ኢየሱስ በሮሜ ውስጥ የተጻፈውን ድነት እግዚአብሔር ያከናወነበት ሰው መሆኑን ነው።

ስለዚህ በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ የቡድኑ አባላት ከወንጌላት መካከል አንዱን እንዲያነቡ እንጋብዛቸዋለን። ይህንንም ከመጀመሪያው ምሽት ይልቅ በሁለተኛው ምሽት ብንነግራቸው ይሻላል። በተለይም የሉቃስ ወንጌል የጌታችንን ሕይወት በሙሉ ስለሚያቀርብ እንዲያነቡት እንመክራቸዋለን። በሚገባ ማንበብ ለማይችሉ አጭርም ስለ ሆነ የማርቆስን ወንጌል እንዲያነቡ ብናደርግ የተሻለ ነው። ያም ሆነ ይህ መጽሐፉን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እንዲያነቡት ያስፈልጋል። ያላንዳች ጥርጣሬ፥ ሰዎች ወንጌልን እንዲያውቁ እንሻለን ፤ (ይህ ከሮሜ ጥናትን እንጻር ነው)፤ ከክርስቶስ ጋር እንዲተዋወቁም እንሻለን፤ (ይህም ወንጌልን ከማንበባቸው የተነሣ ነው)። እውነቱን ልናሳያቸው፥ ደግሞም ስለ ሰውነቱ ልናስተዋውቃቸው ያስፈልገናል። የመስቀሉን ፅንሰ ሐሳብ ማስገንዘብ ብቻ ሳይሆን በመስቀሉ ላይ የሞተውን ሰው እናስተዋውቃቸዋለን።

## የተገለጠ የድነት ዕቅድ

አንድ ጊዜ የሮሜን ዋና ዋና ሐሳብ በተሰባሰበ ይዘት ለሰዎች ካብራራን በኋላ ከምዕራፍ 1 ቍጥር 18 ማንበብ እንጀምራለን፤ በዚህ ስፍራ ሐዋርያው ጳውሎስ ደረጃ በደረጃ እግዚአብሔር ስለ ድነት ዕቅድ የፈጸመውን ያብራራል። ምንም እንኳ ለቤተ ክርስቲያን በምናቀርበው ስብከት ላይ ባናደርገውም ፈጠን ብለን ወደ ፊት እንሄዳለን። በዚህ ጊዜ ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለውይይት የቀረቡትን ስልቶች እናገኛለን፤ (ከምዕራፍ 8-11 ይመ.)። በአስቸጋሪ ቃላት ወይንም ጠቅሶች እንዳንቸገር አድርገን፥ ምንባቡን በተቻለ መጠን በነጻነት እናነባለን። ሰዎች ቀላል ገለጻና አተረጓጐም ይፈልጋሉ። እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ማስተማር የፈለገውን ነጥብ በነጥብ እንናገረዋለን።

ይህን ነጻ የንባብ መንገድ በምናነብበት ጊዜ ሰዎች ከሐዋርያው ጋር በሐሳብ አብረው እንደሚጓዙ ይሰማቸዋል። ጥያቄ ስናቀርብላቸውም ራሳቸው ፈቅደው ያለመገደድ አስተያየታቸውን ይሰነዝራሉ። በጥናታችን ወቅት ፈጠን ብለን ወደ ምዕራፍ አንድ መጨረሻ በምንጓዝበት ጊዜ ከፍተኛ የሆኑ ኀጢአቶች የእግዚአብርን ፍርድ መቀበል እንደሚገባቸው ማስተዋል ይችላሉ። ይሁን እንጂ ሁላችንም በደለኞች ስለሆንን ጥቃቅን ኀጢአቶች ይቅርታ ይገባቸዋል ብለን የምንገምታቸውን የኀጢአት ዐይነቶችም መመልከት እንዲችሉ እናግዛቸዋለን። አሉባልታና ቅንዓትም ልክ ነፍስ እንደ ማጥፋትና እንደ ማመንዘር ኀጢአት ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚገባቸው ኀጢአቶች ናቸው።

ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ክርስትያኖችን የሚከሱበት አንዱ ኀጢአት ግብዝነት ነው። ስለሆነም በምዕራፍ 2 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያወግዘው

ማየት አንባቢዎቹን ያረካቸዋል:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕግሥት በሚፈታተኑበት፥ የጎሊናን ድምፅ ችላ በሚሉበት እንዲሁም ደነትን ለማግኘት በሕግ በሚመኩበት ወቅት የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚደርስባቸው ሐዋርያው አክሎ ያስጠነቅቅና፥ በምዕራፍ 3 መጀመሪያ ላይ ለአሁኖቹ አንባቢዎቻችን እጅግም አስፈላጊ ያልሆነ ክርክር ከአይሁድ ጋር ይከራከራል:: ከዚያም ጎላ ያሉ ሐሳቦች ወደ አሉበት ወደ ቊጥር 19-20 ያመራል:: እኛ ሁላችን በእግዚአብሔር ፊት ኀጢአተኞችና በደለኞች ስለ ሆንን ከእርሱ ቅጣት ራሳችንን ለማዳን ምንም ማድረግ እንደማንችል በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተገለጠ መሆኑን ትኵረት ልንሰጠው እንችላለን::

ምዕራፍ 3 ቁጥር 20ን ከሁለተኛው ጥናታችን በፊት መድረስ አለብን፣ ቀጥሎ የሚኖረው ጥናት ባብዛኛው በቀረው ምዕራፍ 3 ላይ ይሆናል:: የዚህ ምክንያቱ የእግዚአብሔር የማዳን መንገድ የተብራራው እዚህ ላይ ስለ ሆነ ነው:: እግዚአብሔር ከተስፋ ቢስነት አድኖ እንዴት አድርጎ ከራሱ ጋር እንዳስታረቀን ለማሳየት እያንዳንዱን ጥቅስ በጥንቃቄ ማጥናት አለብን::

ይህ ክፍል ሰዎች በሥራ ሳይሆን በእምነት ስለ መዳን የሚያነሧቸውን ጥያቄዎች በመጥቀስ አብራርቶ ትምህርት ይሰጣል:: ስለዚህ በዚህ ክፍል ላይ ክርክርና ውይይት እንዲነሣ ዕድል መስጠት አለብን:: አስፈላጊ ከሆነ ምዕራፍ 4 ፈጠን ብለን ስለምንሄደው ጊዜያችን ቢዛባ ሊያስጋን አይገባም:: ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ 4 ላይ የገለጻቸውን ሰዎችና ሁኔታዎች ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሰዎች እምብዛም ላያውቋቸው ይችላሉ:: በእነዚህ ነጥቦች ላይ ዝርዝር መግለጫ በመስጠት በሰዎቹ ላይ ውዥንብር ማስከተል የለብንም:: ወደ ምዕራፍ 5 ስንመጣ እንደገና ዝግ ማለት አለብን::

## የምላሽ አስፈላጊነት

የምዕራፍ 5 መጀመሪያ አጋማሽ ለክርስቲያኖች የማረጋገጫ መብት ይሰጣቸውና በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ወዳለው መሠረት ይመልሰናል:: የሮሜን መልእክት ማጥናት እንደቀጠልን የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለ ተማሩት ትምህርት የግል አስተያየታቸውን መስጠት የሚያስችሏቸውን ነጥቦችን እንፈልጋለን:: ወንጌልን ከመረዳታቸው በፊት ግን ይህን አናድርግ፣ ለመገንዘባቸው እርግጠኞች ከሆንን ይህን ከማድረግ ወደ ኋላ አንበል:: በውስጣቸው ስላሉት ግጭቶች ደግሞም መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ፈጥኖ እንደሚሠራ ሊሰማን ይገባል::

የጥናት ቡድኑ ራሳቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው መስጠት እንዳለባቸው ጠንክር አድርገን ገና ያላሰብናቸው ከሆነ የምዕራፍ 5 ሁለተኛ ክፍል ይህን ለማድረግ ጥሩ ዕድል ይሰጠናል:: ሰዎች በተፈጥሯቸው ክርስቲያኖች አይደሉም:: የዚህ ተቃራኒዎች ናቸው:: ስለዚህ በተፈጥሮ ሁላችንም ኀጢአተኞች በመሆናችን

ፍትሐዊ የሆነ ፍርድ ተፈርዶብናል:: ይሁን እንጂ ክርስቶስ ሞቶ ተነሥቶ ከቅጣት አድኖናል:: በዚህም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያቀደውን ሕይወት ሰጥቶናል:: ይሁን እንጂ የክርስቶስን ሥራ ልንቀበል የምንችለው በእምነት ነው:: በመልካም ሥራችን ድነትን ለማግኘት የመሻትን ሙከራ ማውገዝና እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት የቸረንን ስጦታ መቀበል አለብን:: በሥነ ተፈጥሮ ሁላችንም የአዳም ዘሮች ነን:: በአንጻሩ የክርስቶስ ዝርያዎች (ወገኖች) የምንሆነው በእምነት በጸጋው ብቻ ነው::

ይህንን ሐቅ ለጥናት ቡድኑ በምናብራራበት ጊዜ አጠገባችን ባስቀመጥነው ማስታወሻ ደብተር የመጠቀም ጥሩ ዕድል አለን:: «አዳም» ፥ «ክርስቶስ» የሚሉ ሁለት ርእሶችን የያዙ ሁለት ዐምዶችን ማዘጋጀት እንችላለን፤ ሐዋርያው ጳውሎስ እኛ በተፈጥሮ ምን እንደሆንን፥ በአኪያው ደግሞ በክርስቶስ ምን እንደሆንን የገለጸባቸውን ጥንድ የሆኑ የማነጻጸሪያ ቃላት ልንጽፍ እንችላለን:: በዚህ መንገድ ሰዎች ተለዋጩን ሁኔታ ማስተዋል ይችላሉ:: ክርስቶስንና ሥራውን ተቀብለው የዘላለም ሕይወት ማግኘት ከፈለጉ በእምነት የሚያደርጉትን መፈጸም አለባቸው::

ሰዎች እግዚአብሔር አንድ ነገር እንዲያደርግላቸው ሲፈልጉ ወይም በፊቱ ሞገስ ማግኘትን ሲሹ አንድ ዓይነት ወሮታ ሊከፍሉት ወይም በጎ ሥራ ፈጽመው ሊቀርቡት ይሞክራሉ:: ታዲያ ይህን የመሰለ የተዛባ ሰብአዊ አስተሳሰብ ለሰዎች እምነት ዕንቅፋት ይሆንባቸዋል:: የዋህነታቸው ነው እንጂ በጎ ሥራ ድነትን ሊያስገኝ አይችልም:: እንዲህ እያለ የሮሜ መልእክት መሠረታዊ እውነታ ድነት የሚገኘው በጸጋ በእምነት አማካይነት ወደሆነው ትምህርት መልሶ ያመጣናል:: በአንድ ወቅት ብዙ ሰዎች ይህን እውነታ ተቃውመው ነበር:: የተቃውሟቸው መነሻ ይህን የመሰለ ትምህርት ሰዎችን ለኀጢአት ይገፋፋቸዋል በሚል ነበር:: ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ 6 ላይ በሰጠው ትምህርት ክርስቲያኖች ኀጢአትን እንዳይሠሩ ግዴታ እንዳለባቸው ይናገራል:: ይህም ክርስቲያኖች ሕይወት ለሌለው ድንጋጌ ባርነት ራሳቸውን ይሰጣሉ ማለት አይደለም፤ (ምዕራፍ 7):: ይልቅስ እንዲህ ማለት በውስጣቸው ያለው መንፈስ ሕይወታቸውን እንደ ገና እንዲቀርጸው ይፈቅዱለታል ማለት ነው፤ (ምዕራፍ 8)::

## በእግዚአብሔር ኀይል መታመን

ተግባራዊ ጥናታችን እየተጓዘ እዚህ ላይ ደርሷል:: ዓላማውም የሮሜን መልእክት መተርጐምና ማብራራት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ለግል የወንጌል ሥርጭት እንዴት ልንጠቀምበት እንደምንችል እኛን ለማስተማር ነው::

ለዚህ ተግባር መሳካት በተለይ ይህ ዘዴ ነው ብለን የምናስቀምጠው ፎርሙላ የለም:: ከሰዎች ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስላካሄድን ብቻ ንስሐ ገብተው ሊያምኑ አይችሉም:: ለምንዋጋቸው ኀይላት አነስተኛ ግምት መስጠትም

አይገባንም፤ እነርሱ ሥጋና ደም ሳይሆኑ የማይታየው ዓለም ክፉ መናፍስት ናቸው፤ (ኤፌ. 6፥12:: በአንጻሩ የጦር መሣሪያወቻችን የክፉዎቹን መናፍስት ጎራ የሚያፈራርስ፥ መለኮታዊ ኀይል አላቸው፤ (2ቆሮ. 10፥4):: ለእግዚአብሔር የምንፈጽመው ማንኛውም ሥራ መስዋዕትነትን የሚሻ ቢሆንም ዕለታዊ ጸሎት ባይጨመርበት ጊዜያችንንና ጥረታችንን ያለ ፍሬ በከንቱ እናባክናለን:: እኛ ማንንም ማዳን አንችልም፤ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው::

ይሁን እንጂ ወንጌልን የሚሠራበት ተግባር ኀላፊነት እግዚአብሔር የሰጠው ለእኛ ነው፤ ስለዚህ ለጠፋት ነፍሳት ስለ ድነት ለማስተማር በመጽሐፍ ቅዱስ ለመጠቀም ማቅማማት የለብንም:: የሐዋርያት ሥራ ክርስቲያን ስላልነበረው ኢትዮጵያዊ ይተርካል:: ጃንደረባው እውነትን ይሻ ነበር፤ ፊልጶስ ይህ ሰው ያነብ የነበረውን ያስተውል እንደ ሆነ ሲጠይቀው «... የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?» አለው:: (ሐዋ. 8፥30-31):: ሰዎች አሁንም ቢሆን እውነትን ለማግኘት ይሻሉ፤ ይመራመራሉ:: እኛ ግን የሚፈልጉትን እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኝ እናውቃለን:: ግን ራሳቸው በራሳቸው እንዲያነቡና እንዲደርሱበት ብንተዋቸው፥ የሚያነቡትንም ባናብራራንላቸው እውነትን መረዳት አይችሉም፤ ይህን ማድረግ ታዲያ የእኛ ሥራ ነው::

«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፤ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤ ነፍስንና መንፈስን፥ ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ ድረስ ይወጋል፤ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል»፤ (ዕብ. 4:12):: ቃሉ ይህን ማድረግ የሚችለው አንባቢዎቹ የሚያነቡትን ሲገነዘቡ ብቻ ነው:: እኛ የምናምነው ቃሉን በትክክልና በግልጽ የምናብራራበትን መንገድ አስበን ማመቻቸት አለብን:: ይህን ስናደርግም የምንሰጠው ማብራሪያና ትምህርት በሰዎች ልብ ውስጥ ሊሠራ እንደሚችል በማመን ጭምር መሆን አለበት::

### ተጨማሪ ሐሳቦች

አብዛኛውን ጊዜ የጥናቱ ተሳታፊዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸውን በስድስት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ አጥንተው የሮሜን መልእክት ማጠቃለል ይፈልጋሉ:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ከወንጌላቱ መካከል አንዱን አንብበው ስለሚጨርሱ ከዚያ በማያያዝ የሐዋርያት ሥራን ጥናት መጀመር እንችላለን:: ይህም ከወንጌላት የቀጠለ ትረካ የያዘ በመሆኑ ስለ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መስፋፋት ትምህርት ሊሰጣቸው ይችላል:: ከሁሉም በላይ ክፍሉ ወንጌልን ሰለ ማስፋፋት መልእክት አለው፤ ይህም የወንጌልን የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ያሳያል:: በወንጌላት ውስጥ ሰዎች ክርስቶስን በሕይወቱ፥ በሞቱና በትንሣኤው አይተውታል፤ በሮሜ መልእክት ሥራው ኀጢአተኞችን እንዴት እንዳዳናቸውና ከእግዚአብሔር ጋር እንዳስታረቃቸው ያስተውላሉ፤ በሐዋርያት ደግሞ ሰዎች የኢየሱስን መልእክት ተቀብለው በንስሐ፥ በእምነትና በጥምቀት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ያያሉ::

በዚህ ሂደት ውስጥ አንዳንድ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ቢገነዘቡም እንኳ ለወንጌል ምላሽ ለመስጠት ጊዜ የሚወስድባቸው መሆኑን እንገነዘባለን:: የሮሜን መልእክት በምናጠናበት ጊዜ እንዲዚሁ ራሳቸውን ለክርስቶስ ስለመስጠታቸው ባይገልጹ፥ የሐዋርያት ሥራን በምናጠናበት ጊዜ ይህን ለማድረግ ሊቀሰቀሱ ይችላሉ::

የጥናቱ ቡድኖች ይህን ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ አብረውን ተጕዘው እዚህ ከደረሱ በቂ ዕውቀት እንዳገኙ አድርገው ራሳቸውን አይቈጥሩም:: እንዲያውም መረጋጋት ይታይባቸዋል:: ስለዚህ ክርስትናን በተመለከተ ወደ ሌላ ትምህርት ልንወስዳቸው እንችላለን፤ እንዲህ የምናደርገው ግን ቀደም ሲል ያልፈጸምነው ትምህርት ካለ ነው:: ተሳታፊዎቹ ፈቃደኞች ከሆኑ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ነጥቦችን በመጥቀስ የጀመርነውን ትምህርት በጸሎት እንድንዘጋ እናስታውሳቸዋለን:: ወደ ቤተ ርስቲያን የማይሄዱ ከሆኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወይም ወደ ሌላ ተስማሚ የክርስቲያን ስብሰባ እንዲመጡ እንጋብዛቸዋለን:: እንዲሁም ግንዛቤያቸውን በማዳበር የሚያግዟቸውን ለምሳሌ ስለ ቤተ ሰብ፥ ስለ ማኅበራዊ ሕይወትና ስለ አካባቢ ሁኔታ የሚያወሱ መጻሕፍትን እንሰጋሳቸዋለን፤

የክርስቲያን መጻሕፍትን በተመለከተ እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሪዎች ሳንቀር በስፋት ማንበብ አለብን:: ባነበብነው ስፋት መጠን የምናነሣቸውን ጥያቄዎችም ሆነ የምንጠይቀውን ጥያቄ አጥጋቢ በሆነ መንገድ በልበ ሙሉነት መመለስና ማስረዳት እንችላን፤ ውይይትም ብናካሄድ ፍሬያማ በሆነ መንገድ እስተዋጽኦ እያደረግን መምራት አያቅተንም::

ከላይ በተሰጠው አጠቃላይ ሁኔታ መሠረት የሮሜን መልእክት ለመምራት በራስ መተማመን ከሌለን ለሥራችን በሚያግዘን የታተመ ጽሑፍ መጠቀም እንችላለን:: ለዚህ ሊያግዘን የሚችልና በጣም ተስማሚ የሆነው «ክርስቲያንነት» ሲብራራ የሚለው መጽሐፍ ሲሆን ይህም በማይክል ቤነት የተደረሰና በስክሪፕቸር ዩኒየን የታተመ ነው:: በስድስት ጥናቶች መርሐ ግብር ውስጥ ተሳታፊዎች የማርቆስ ወንጌል ሊያነቡ ይችላሉ፤ እነዚህም 1. ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ፥ 2. የኢየሱስ ስቅለት፥ 3. የኢየሱስ ትንሳኤ፥ 4. ድነት በጸጋ፥ 5. ንስሐና እምነት፥ 6. ዋስትና (ማረጋገጫ) ናቸው::

ሰዎች ወንጌልን በመስማታቸው ውጤታቸውን በንስሐና በእምነት ቢገ[illegible] ይህን ከሰው ወደ ሰው የምናደርገው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች [illegible] እንዳንመለከተው፡ ከዚያ ወደ ሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትና [illegible] ወደ ሆኑ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መሄድ አለብን፡ በዚህም አዲስ አ[illegible] ስለ [illegible] ባላቸው ዕውቀት እንዲያድጉ እንረዳቸዋለን:: ይህም በራስ መተማመን[illegible] ስ[illegible]ቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሌሎች ቡድኖች አባላት ሲሆኑ ወይም በቤተ [illegible] ውስጥ ለሕዝብ የሚሰጠውን ትምህርት ሲሰሙ ብቸኝነት አይሰማቸውም፡ አላዋቂም አይሆኑም:: ጥሩ መሠረት አንድ ጊዜ ከተተከለ በዚያ ላይ ሊገነቡ ይችላሉ::

# ፲፬

## እያሻሻሉ መራመድ

### የመንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቅም

እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት እግዚአብሔር የሰጠንን መንፈሳዊ ስጦታዎች የምናሳድግበት መንገድ በእነርሱ መጠቀም ነው፤ (ሮሜ 12÷6)፡፡ ሆኖም ሥርዐት ባለው ሁኔታ ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ስጦታዎችን የሚለግሥን ለግላችን ደስታ ወይም ርካታ እንድናውላቸው ሳይሆን ሌሎችን ለመጥቀምና ለመገንባት እንድንጠቀምባቸው ነው፡፡ ስጦታዎች የሚሰጡት ለጋራ ጥቅም (1ቆሮ. 12÷7)፥ ቤተ ክርስቲያንን ለማበረታታት ነው፤ (1ቆሮ 14:5-2)፡፡ ነገር ግን በቅናትና በራስ ወዳድነት መንፈስ በተግባር ላይ በሚውሉበት ጊዜ ክፉ ተግባርና ምስቅልቅልነት ይከሰታሉ፤ (ያዕ. 3÷16)፡፡ ያለ ትሕትናና ያለ ፍቅር የሚፈጸም የመንፈስ ስጦታዎች ልምምድ በአደጋ ላይ ይወድቃል፡፡

ስለዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን ለመለማመድ ፍላጎት እንዳለን ሁሉ ፍቅርን በተግባር ላይ ለማዋል ልምምዱ ሊኖረን ይገባል፤ (1ቆሮ. 14÷1)፡፡ ያለ ፍቅር ሁላችንም ምንም አይደለንም፡፡ ምናልባት በስብከት ወቅት ድምፃችን ድንቅ ሆኖ ይሰማ ይሆናል፤ ነገር ግን ከሚጮህ ናስና ከሚንሿሿ ጸናጽል አይበልጥም፤ (1ቆሮ. 13÷1)፡፡ ይህ አባባል ስጦታዎቻችንን ለማሳደግ ጠንክረን እንዳንሠራ ዕንቅፋት አይሆንብንም፤ በአንጻሩ ስሜታችንንና ባሕርያችንን በማዳበር ጠንክረን እንድንሠራ የሚያበረታታን ነው፡፡

### ስልትና ዘዴ

ስጦታዎቻችን እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋ መጠን ይለያያሉ፤ (ሮሜ 12÷6)፡፡ ሁላችንም ወደ መብሰል እንድንመጣ ስጦታዎች ያስፈልጉናል፡፡ የተለያየ የስብከት ዘዴ ይኖረን ይሆናል፤ ሁላችንም ግን የስብከታችንን ስልት ለማሻሻል በርትተን መሥራት አለብን፡፡

ጢሞቴዎስ በሕዝብ ፊት እንዲሰብክ ብቁ ያደረጉት መንፈሳዊ ስጦታዎች ነበሩት፤ ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ስጦታዎች እንዲያነሣሣ አሳስቦት ነበር፤ (1ጢሞ. 4÷13-14)፡፡ ሌሎች ዕድገቱን ማየት እንዲችሉ ይህን በትጋት እንዲፈጽም ያበረታታው ነበር፤ (1ጢሞ. 4÷15)፡፡ የጢሞቴዎስም አገልግሎት ፍሬያማ እንዲሆን ባደረገው ጥረት መጠን ለራሱ መንፈሳዊ ሕየወትም ይጠነቀቅ ነበር፤ (1ጢሞ. 4÷12፣16)፡፡ ስጦታዎቹን ለማሳደግም መንፈሳዊ ሕይወቱን ማሳደግ

ነበረበት። እኛም እንደ ጢሞቴዎስ የስብከታችንን ጥራት ለማሻሻል ሌሎች ሊያዩት በሚችሉት አኳኋን ማራመድ እንድንችል ሳናቋርጥ መሥራት አለብን።

አንድ ጊዜ ስብከታችንን ማሻሻል ማለት ስለ እኛ የተቀረጸ ቴፕ ማዳመጥ እንደማለት ነው። ይህን ማድረግ ካልቻልን ከቅርብ ወዳጆቻችን ወይም ከአድማጮቹ መካከል ካሉ ሰዎች አስተያየት መቀበል ይኖርብናል። ንግግራችን በጣም ፈጣን ወይም ዘገምተኛ፥ ደረጃውን የጠበቀ ወይም የወረደ ቢሆን፥ የቃላትን መጥበቅና መላላትን ባንጠብቅ፥ መዝሙር ብንዘምርና ድግግሞሽ ቢኖር፥ ስብከታችን የሚወደድና ምስጋና ለማግኘት የሚዳርግ ከሆነ ወይም ከባድ ቃላት ካሉበት፥ በንቃት ሳናቋርጥ ከስሕተታችን ለመማር መጣር አለብን። በየጊዜው ቀረጻ ማካሄድ አለብን። ይህን ማድረግ እያሻንም በምንልበት ጊዜ ቢሆን እንኳ ይህን ማድረግ አለብን። ምክንያቱም አንድን መጥፎ ነገር ሳናስወግደው ሌላው ስለሚከተል ነው።

በቪዲዮ የተቀረጸ ስብከታችንን ብናዳምጥ ከዚህ ብዙ መማር እንችላለን፤ ነገር ግን ብዙዎቻችን ይህን የመሰለ ዕድል የምናገኘው አልፎ አልፎ ነው። ይሁን እንጂ እኛን በመከታተል ስላዩት ሁኔታ አስተያየታቸውን በመስጠት ሊረዱን የሚችሉ ጓደኞች አሉን። ታዛቢዎች የሚሰጡንን አስተያየት በጸጋ መቀበል አለብን። ምክንያቱም እነዚህ አስተያየቶች እንደ መቁነጥነጥ፥ መወዛወዝ፥ ፋይዳ ቢስ የአካል እንቅስቃሴ፥ ሐሳብን የሚበታትን ጠባይ፥ እንደዚህ ያሉትን መጥፎ ልምዶች ተዋግተን ድል እንድናደርግ ይረዱናል። በአንድ በኩል ፊታችንን ከመቋጠር በሌላ በኩል ያለምክንያት ጥርሳችንን ከመገልፈጥ መጠንቀቅ አለብን። ከአድማጮቻችን ጋር ግንኙነት ለማድረግ ዐይን ለዐይን መተያየት እንችላለን፤ ሆኖም ለይተን ወደ አንድ አቅጣጫ ማዘንበልን እንቈጣጠር።

ሌሎች ሰባኪዎች በሚሰብኩበት ጊዜ በመመልከት መልካሙን ከመጥፎ ለይተን መውሰድ ወይም ማረም እንችላለን። ሆኖም ሌሎች የሚያደርጉትን መኰረጅ የለብንም፤ የምናደርግ ከሆነ ግን አድማጮቻችን ምን እንደምንሰብክ ይረዱትና ማዳመጥ ይሳናቸዋል። ስለአሰባበካችን ዘዴ ማንም ሰው ሊሰጠን የሚቻለው ምክር «ራሳችሁን ሁኑ» የሚል ነው። እንዲህ ማለትም የራሳችን ማንነት የስብከታችን ማዕከል ይሁን ማለት እንጂ መጥፎ ልምዳችንን አንለውጥ ማለት አይደለም፤ መልካም ዘዴን ለማዳበር አሻፈረን እንላለን ማለትም አይደለም፤

## ስለ ቃላት ማሰብ

በቤ ተክርስቲያን ውስጥ ስንሰብክ ለምንጠቀምባቸው ቃላት ማሰብ እንዳለብን ቀደም ሲል ጠቅሰናል። እነዚህም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስፋት የሚነገሩ፥ በየቀኑ በሚደረገው ንግግር ውስጥ ግን የማይገኙ ማስወገድ የሚገባን ከባድ ቃላት ናቸው፤ (ምዕራፍ 5 ይመ.)። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስለማይሄዱና

ክርስቲያን ስላልሆኑ ሰዎች ትምህርት ጉዳይ (ምዕራፍ 13 ይመ.)። በእነዚህ ሰዎች ዘንድ ለምንጠቀምባቸው ቃላት በጥንቃቄ ማጥናት ያስፈልገናል። ክርስቲያኖች ቀላልና ቀጥተኛ በሆነ፥ በተለመደ ቋንቋ መናገር አለመቻላቸው ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እምብዛም ግድ የሌላቸው እንዲሆኑ ካደረጓቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው።

ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችን በምናስተምርበት ጊዜ ለምሳሌ «መልእክት» ባማለት ፈንታ «ደብዳቤ» ፥ «ቅዱሳት መጻሕፍት» በማለት ፈንታ «መጽሐፍ ቅዱሴ» ማለት ይሻላል። «መጽሐፍ ቅዱስ» ወይም «ቅዱሳት መጻሕፍት» ብንል ስሕተተኞች አይደለንም፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች ብቻ የሚገነዘቧቸውን ቃላት በመምረጥ ፈንታ ማንኛውም ሰው የሚገነዘባቸውን መምረጡ የበለጠ ነው።

ትምህርተ መለኮትን የሚመለከቱ ነገሮችን ማብራራት አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ሐሳባችንን በቀላል መንገድ ለመግለጽ ባሰብን ቍጥር ግንዛቤአችንንም እንደዚያው እናሻሽላለን። ስለ ጥንቃቄ ማሰብ ትክክለኞች እንድንሆን ይረዳናል። ከሥላሴ ጋር የተያያዘ አስቸጋሪ ጉዳይ ቢያጋጥመን እንኳ በተቻለ መጠን ውስብስብ እናድርገው። ብዙ ሰዎች በ «እግዚአብሔር» ፥ «ጌታ» ፥ «ያህዌ» ፥ «ክርስቶስ» ፥ «ኢየሱስ» ፥ «መንፈስ ቅዱስ» መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ይደበላለቅባቸዋል። እነዚህ ቃላት አንድ ወይም የተለያዩ ይሁኑ እርግጠኞች አይደሉም። ስለዚህ ለመናገር ስለምንፈልገው ነገር እርግጠኞች መሆን አለብን። ብዙ ትርጕም ባላቸው ቃላት መጠቀምም አይኖርብንም፤ ለምሳሌ «ጌታ» በሚለው ፈንታ «ኢየሱስ» ማለት ብንፈልግ በዚሁ መጠቀም አለብን፤ ወይም «እግዚአብሔር» በሚለው ቃል መጠቀም ብንፈልግ በዚሁ እንጠቀም። ሰዎች አንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ከሆኑ መላውን ነገር ልንገልጽላቸው እንችላለን።

በልምምድ ቴክኒካዊ ቃላትን ማሳደግ እንችላለን፤ ነገርችን ለመግለጽ ቀላል መንገድ እንፈልጋለን፤ ራሳችንን ለመግለጽም አያዳግተንም፤ ጠቃሚ የሆኑ ምሳሌዎችንና መረጃዎችን እንዲሁም ማነጻጸሪያዎችን የማሰባሰብ ሁኔታዎችን እናዳብራለን። የተማሪነት ዝንባሌ ካለን ልንናገራቸው ወይም ላንናገራቸው የሚገባንን ለይተን ማወቅ እንችላለን።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምንሰበሰብበት ጊዜ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በምናስተምርበት ሁኔታ በንግግራችን ላይ ቍጥቦች ልንሆን አንችልም። ሆኖም ወደ እርሷ ልምምዳችን ተንሸራተን እንዳንወድቅ መጠንቀቅ አለብን። የምንናገራቸው ቃላት ለእኛ ያላቸውን ትርጕም ለአድማጮቻችን ይሰጡ እንደ ሆነ ሁልጊዜ መመርመር አለብን። ይህን ማድረግ የምንችልበት አንዱ መንገድ በምእመኑ ውስጥ ስላሉ አንዳንድ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችን ዘግባቡና የምንናገረውን ይገነዘቡ እንደ ሆነ በጎሊናችን ውስጥ መገመት ነው።

**ሰውየውና መልእክቱ**

በምናስተምርበት ጊዜ ቃላትን በመምረጥ ከምናደርገው ጥንቃቄ ሌላ ስለንግግራችንና ስለ ጠባያችን ጠቅላላ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:: ሰዎች የእግዚአብሔርን ባሪያዎች ለውግዘት የማያደርስ ንግግር መናገር አለባቸው፤ (ቲቶ 2፥8 ፤ ቆላ. 4፥6)፤ በሰዎች ዘንድም ሆነ በግል ሕይወታቸው ነውር የሌለባቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፤ (ቲቶ 1፥6-7 ፤ ፊል 2፥15):: ስለዚህ አኗኗራችን ከምናስተምረው ትምህርት ጋር የሚስማማ መሆን አለበት::

ይህን የማድረግ ጉዳይ የማያቋርጥ ንቃትንና ሥነ ሥርዐትን ይጠይቃል:: ምክንያቱም በአንድ በጐላ ስሕተት አድማጮቻችን የትኛውንም ንግግራችንን እንዳያዳምጡ ይዳረጋሉ:: ይህም ከእግዚአብሔር ዘንድ ከባድ ፍርድ ሊያመጣብን ይችላል:: ሐዋርያው ያዕቆብ፥ የሚያስተምሩ ከሌሎች በበለጠ ይፈረድባቸዋል ይላል፤ (ያዕቆብ 3፥1):: ሐዋርያው ጳውሎስም በሌሎች እየፈረድን የሚያደርጉትን ነገር ብናደርግ ራሳችንን እንደምንኰንን ይናገራል፤ (ሮሜ 2፥1)::

ምንም እንኳን ይህን ማስጠንቀቂያ ከልብ ብንቀበለውም ከፍርሀት ወይም ድፍረት ከማጣት የተነሣ እግዚአብሔር የሰጠንን ኀላፊነት ሳንወጣ መቅረት የለብንም:: እግዚአብሔር ለሰጠን ዐደራ ለምንሰጠው ምላሽ ሁሉ ተጠያቂዎች ነን፤ ስለዚህ የምናከናውነውን ተግባር ከልብ፥ በታማኝነትና በማስተዋል ማድረግ አለብን፤ (1ቆሮ. 4፥1-2):: ከዚሁ ጋር በእግዚአብሔር ላይ የምናደርገው መደገፍ በጸሎት መታገዝ አለበት:: ሰዎች ወደ እግዚአብሔርና ወደ ቃሉ እንዲሳቡ እንጂ ወደ እኛና ወደስብከታችን ስልት እንዲሳቡ አንፈልግ:: ስበከታችንና ትምህርታችን ልብን ለውጦ ወደ እምነት በሚያመጣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ አለበት:: ይህ ሲሆን አድማጮቻችን ልባቸውን በሰዎች ስኬቶች ላይ በመጣል ፈንታ በእግዚአብሔር ኀይል ላይ ያሳርፋሉ፤ (1ቆሮ. 2፥4-5)::

**የመጨረሻው ፈተና**

አገልግሎታችን በጠንካራ ሥራና በጸሎት ሲታገዝ ለእግዚአብሔር ክብር፥ ለአድማጮቻችን ጥቅም ይሆናል:: በአሰባበካችን ዘይቤና ስልት ተግባራዊ ለሆነ መሻሻል እንጥራለን፤ ከሁሉም በላይ ግን ሰዎችን በእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት ለመገንባት ዐላማ ሊኖረንና፥ በትምህርታችንም ምሳሌያዊነትንና መጋቢያዊነትን ልናካትት ይገባል::

ይህን በአእምሯችን በመያዝ የስብከታችን ይዘት ሁልጊዜ ሊያሳስበን ይገባል:: ማለፊያ ይዘት ያለውና በሚስብ ሁኔታ የቀረበ ስብከት ካዘጋጀን ለሠላሳ ደቂቃ ወይም ከዚያ በላይ ለረዘመ ጊዜ አድማጮቻችንን ይዘን ለመቆየት

አያቅተንም:: በደንብ ያልተዘጋጀና የማይስብ ስብከት ለዐሥር ደቂቃ እንኳ ቢቀርብ ለረጂም ጊዜ የቀረበ ይመስላል::

የጥሩ ስብከት ፈተና ውጤት ሰዎች ከስብከቱ በኋላ የሚቸሩን ምስጋናና ውዳሴ ሳይሆን፣ በሕይወታቸው ውስጥ የሚያስከትለው ውጤት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሰጠነው ማብራሪያ ግቡን መታ የምንለውም አድማጮቻችን ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቁ፥ ወደ ክርስቶስ መልክና ምሳሌ ሲለወጡ ነው:: ዐላማችን ሰዎች በእኛ ወይም በስብከታችን ላይ እንዲደገፉ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት አድርገው ሊመገቡ እንደሚችሉ ማስተማር ነው:: ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤታቸው ሲመለሱ መጽሐፍ ቅዱስ የተናገራቸውን ለመፈጸም ወስነው እንዲመለሱና በውስጣቸው የተደረገውን ተሐድሶ እንዲያስተውሉ ማስገንዘብ አለብን:; ይህን ማድረግ በሚጀምሩበት ጊዜ መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎች እርሱን መከተል ትተው ኢየሱስን መከተል በጀመሩበት ጊዜ የተሰማው እርካታ ዐይነት እኛንም ይሰማናል:: ምክንያቱም ቃሉ ሊልቅ እኛ ግን ልናንስ ይገባናል፤ (ዮሐ. 3፥26-30)::